ነበር። ሊጉ ምዝገባ እንዲፈጸም የፍርድ ቤት ትእዛዝ ቢያገኝም፣ መንግሥት ለምዝገባ ጥያቄው መልስ አልሰጠም።

መንግሥት ከዓለምአቀፍ የሰብዓዊ መብት መያዶች ጋር ያለው ግንኙነት በዓመቱ ውስጥ መሻሻል ታይቶበታል። በዓመቱ ውስጥ በርካታ የሰብዓዊ መብቶች ዓለምአቀፋዊ ስብስቦች አገሪቱን በመጐብኘት፣ አስቸኳይ ስብዓዊ እርዳታ የሚያስፈልጋቸውን አካባቢዎች ካለቁጥጥር ማየት ችለዋል። አንዳንድ የአምነስቲ ኢንተርናሽናል ከፍተኛ ደረጃ የልዑካን ቡድን በ10 ዓመታት ውስጥ ለመጀመሪያ ጊዜ አገሪቱን ጐብኝቷል። የአፍሪካ ሕብረት ልዩ ራፖርተር በአገሪቱ ውስጥ በተለያዩ ሥፍራዎች የሚገኙ ማረሚያ ቤቶችን ጐብኝቷል። (ክፍል 1 ሐን ይመልከቱ)። መንግሥት በሰብዓዊ መብት ጉዳዮች ላይ ከሚያተኩሩ ዓለምአቀፋዊ መንሥታዊ ድርጅቶች ጋር ተባብሯል። የፌዴራል ደህንነት ባለሥልጣን ሹማምንት ከዲፕሎማቲክ ማሕበረሰቡ ለሚቀርቡ የመረጃ ጥያቄዎች ከቀድሞ በተሻለ መልስ ሰጥተዋል።

መንግሥት የሰብዓዊ መብቶች ኮሚሽን እና በአስፈጻሚው አካላት ለሚፈጸም የአስተዳደር ጉድለት አቤቱታዎችን የሚቀበል እና የሚመረምር እንባ ጠባቂ አካል እንዲያቋቁም ሕገ መንግሥቱ ይደነግጋል። በነሐሴ ወር መንግሥት ካሣ ገብረሕይወትን የሰብዓዊ መብቶች ኮሚሽነር፣ ዓባይ ተክሌን እንባ ጠባቂ ብሎ ሰይሟል። በዓመቱ መጨረሻ አንዳቸውም ሥራቸውን አሟልተው አልጀመሩም ነበር።

በዓመቱ ውስጥ የፍትሕ ሚኒስቴር በሰብዓዊ መብቶች ላይ የሶስት ዓመት የሥልጠና ፕሮግራም (ወርክሾፕስ) ለዳኞች፣ አቃብያን ሕግ እና ፖሊስ፣ እንደዚሁም የማኅበረሰብ አባላት በመላ አገሪቱ ጀምሯል።

በታኅሣሥ 1995 በጋምቤላ ተፈጥሮ ከነበረው የጐሣ ግጭት ጋር በተያያዘ መንግሥት የሰብዓዊ መብቶችን ተዳፍሮ እንደሆነ አንድ (ፓርላሜንታዊ) ኮሚቲ በዓመቱ ውስጥ መርመራ አካሂዷል። (ክፍል 5ን ይመልከቱ)።

ክፍል 5 መድልዎ፣ ማኅበራዊ ጥቃቶች፣ እና በሰዎች መነገድ

ሕገ መንግሥቱ በዘር፣ በቀለም፣ በጾታ ፣ በቋንቋ፣ በትውልድ፣ በፖለቲካዊ ወይም ሌላ አመለካከት፣ ወይም በማኅበራዊ አቋም መሠረት ልዩነት (መድልዎ) ማድረግን ይከለክላል። ሆኖም፣ መንግሥት እነዚህን ጥበቃዎች በግብር በሚገባ እንዲፈጸሙ አላስገደደም።

ሴቶች

ሚስትን መደብደብን እና በጋብቻ ውስጥ አስገድዶ መድፈርን ጨምሮ፣ የቤት ውስጥ ሁከት የተስፋፋ ማኅበራዊ ችግር ነበር። የቤት ውስጥ ሁከትን ወይም ወሲባዊ ማዋከብን በሚመለከት የተለየ ሕግ የለም። ሴቶች ወደ ፖሊስ እና ፍርድ ቤቶች ቢሄዱም፣ በተለይ በገጠር አካባቢዎች፣ ማኅበራዊ ልማዶች/መመዘኛዎች እና ፍርድ እና የመሠረተ ልማት ውሱንነት የሴቶችን የሕግ እርዳታ ማግኘት አሰናክለውታል። እንደዚሁም አስገድዶ መድፈር በሚደርስበት ጊዜ ሁኔታውን መርምሮ ክስ መመሥረትን ማኅበራዊ ልማዶች ከማሰናከላቸውም ባሻገር፣ ሴቶች በሕግ መሠረት ያሉዋቸውን መብቶችም አያውቁም። በአዲስ አበባ በዓመት ከ1000 በላይ አስገድዶ መድፈር እንደሚፈፀም ተገምቷል። ጋዜጦች የአስገድዶ መድፈርን ሁኔታዎች፣ በተለይም በልጆች ላይ ጉዳት በሚያስከትልበት ጊዜ ሳያሰልሱ መዘገባቸውን ቀጥለዋል። ከ10 እስከ 15 ዓመት በሕግ የተወሰነውን በመከተል በአስገድዶ መድፈር የቅጣት ፍርድ ተሰጥቷል። በዓመቱ ውስጥ ኢሴሕባማ ስንት አስገድዶ መድፈር እንደተፈጸመ እና በስንቱ ላይ ፍርድ እንደተሰጠ ምርምር ቢያካሄድም፣ በዓመቱ መጨረሻ ውጤቱ አልተገለጸም። በዓመቱ ውስጥ በሴቶች እና በሕጻናት ላይ የሚፈጸሙትን ወሲባዊ ድፍረት የሚዳኝ አንድ ፍርድ ቤት ተቋቁሟል። (ክፍል1 ሠን ይመለከቱ)።

ሕገ ወጥ ቢሆንም፣ እንደ አንድ የጋብቻ ዓይነት ሆኖ ሴቶችን እና ልጃገረዶችን መጥለፍን መንግሥት መዋጋት ቢሞክርም፣ በኦሮሚያ እና በደቡብ ክልሎች በሰፊው እንደቀጠለ ነበር። ጋብቻዎች በጠለፋ በሚፈጸሙበት ጊዜ በአብዛኛው የወሲብ ግንኙነትን ካለሴቷ ፈቃድ አስገድዶ መፈጸም ይጣመራል። በጠለፋው ወቅትም ሴቶች በአካል ይደፈራሉ። በሕግ የተወሰነው የጋብቻ ዕድሜ 18 ዓመት ቢሆንም፣ ከእነዚያ ውስጥ ብዙ ልጃገረዶች በ7 ዓመት የጨቅላ ዕድሜ አግብተዋል። ጠለፋ በቤተሰቦች፣ በማኅበረሰቦች፣ በጐሣ ስብስቦች መካከል ግጭቶችን ፈጥሯል። ጋብቻ

በጠለፋ በሚፈጸምበት ጊዜ፣ ተጠቂዋ ልታገባው ከፈቀደች (ጋብቻው ወድቅ ካልሆነ በቀር)፣ አጥፊው አይቀጣም። ድርጊቱን የፈጸመው ጥፋተኛ መሆኑ ቢረጋገጥም፣ ተጠቂዋ ካገባችው እሥራቱ/ቅጣቱ ይቀራል። በሴቶች ለይ የሚፈጸም ጥቃት እና ካለዕድሜ ጋብቻ ችግሮች መሆናቸው በሕዝብ ዘንድ እየታወቀ ስለመምጣቱ አንዳንድ ምልክቶች ነበሩ። በችግሩ ላይ ቅሬታ ለማሰማት በነሐሴ ወር በደሴ ሰላማዊ ሰልፍ ተደርጐ ነበር።

አብላጫዎቹ ልጃገረዶች አንድ ዓይነት ወይም ሌላ ግርዛት የተፈጸመባቸው ናቸው። ግርዛት ሕጻኗ በተወለደች በ7ኛው ቀን የሚፈጸም ሲሆን፣ ይሄም በአንዕስት ብልት በውጭው ጫፍ የሚገኘውን ስሜት የሚሰጠውን ክፍል ቀንጥቦ ማስወገድ ነው። በጣም ከባድ እና አደገኛም የሆነው ግርዛት (ኢንፊቡሌሽን) በ8 ዓመት ዕድሜ እና ለአቅመ ሔዋን መዳረሻ የሚፈጸመው ነው። በ1995 ዓ.ም. በአንድ የመንግሥት የጐጅ ባህሎች እና ልማዶች መሠረታዊ ጥናት ግኝት እንደተገለጸው፣ ከመቶ 90ው ሴቶች ከአራት አንዱ ዓይነት ግርዛት (circumcision, clitorisectomy, excision, and infibulation) ይፈጸምባቸዋል። በመሠረታዊ ጥናቱ መሠረት፣ በሴቶች ላይ የሚፈጸሙ ጐጅ ልማዶች፣ ግርዛትን፣ ጠለፋን፣ እና ለአካለ መጠን ሳይደርሱ መዳርን ጨምሮ፣ ከ1994 ዓ.ም. ወዲህ 90 ከመቶ የነበረው ወደ 73 ከመቶ ዝቅ ማለቱን ጐጅ የሆኑ ባህላዊ ልማዶች ብሔራዊ ኮሚቲ ዘግቧል።

ሕገ መንግሥቱ እና የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ በአካል ላይ ጉዳት ማድረስን ይከለክላሉ። ሆኖም፣ እነዚህ ድንጋጌዎች የሴቶችን ግርዛት ለይተው ሕገ ወጥ አላደረጉትም። በዓመቱ ውስጥ መንግሥት የወንጀለኛ መቅጫ ሕጉን ወቅታዊ በማድረግ ቀጥሎበታል። እንደዚሁም በሕዝብ ትምህርት ቤቶች በሚሰጥ ትምህርት እና በዜና ማሰራጫዎች በተካሄዱ ዘመቻዎች አማካይነት፣ መንግሥት የሴቶች ግርዛት ልማድን ለማዳከም ሠርቷል።

መንግሥት የሴቶችን ግርዛት ለማስወገድ የሚረዱ አንዳንድ እርምጃዎች ወስዷል። ለምሳሌ፣ በደቡብ ክልል አንድ የደቡብ ኦሞ ዞም፣ አንድ የሀመር ወረዳ ዞም ሚስቱን እንድትገረዝ ስላስገደዳት ከኃላፊነቱ መነሳቱን በሐምሌ ወር ገልጿል። ያ የሀመር ዞም ከዚያ በኋላ በወረዳው የሴቶች ጉዳይ ቢሮ ለፍርድ እንዲቀርብ ተደርጓል። የደቡብ ኦሞ ዞን የዝግጁነትና የማኅበራዊ ጉዳይ መምሪያ ምክትል ኃላፊ፣ የጐጅ

ባሕል አስወጋጅ ኮሚቴዎች በዞኑ 197 አካባቢዎች መቋቋማቸውን ዘግቧል። በምሥራቅ ሐረርጌ ዞን በአንድ ቀን 62 ልጃገረዶችን ገርዘዋል ተብለው የተወነጀሉ 4 ሴቶችን ፖሊስ በቁጥጥር ሥር አውሏል። ግርዛት ጉዳቶችን እንደሚያስከትል በዜና ማሰራጫዎች የተጠናከረ ዘመቻ ከተካሄደ በኋላ የአካባቢው ነዋሪዎች ለፖሊስ መጠቆማቸውም ተነግሯል። በዓመቱ መጨረሻ በሴቶቹ ላይ ክስ እንደሚመሠረት እየተጠበቀ ነበር።

በዝሙት ንግድ የተሠማሩ ወገኖች ለሴትኛ አዳሪነት የሚዳርጋቸው መሠረታዊ ምክንያት ድህነት መሆኑን ደጋግመው ዘግበዋል። እድሜያቸው ከ18 ዓመት በታች ለሆነ የተከለከለ ቢሆንም፣ አጠቃላይ ሴትኛ አዳሪነት ሕጋዊ ነበር። አቃጣሪነት እና ከዝሙት ማትረፍም ሕገወጥ ነበሩ። ሴትኛ አዳሪነት ችግር ነበር።

በእንዱስትሪ እና በቤት ውስጥ ሠራተኛነት ወደ መካከለኛው ምሥራቅ የሄዱ ብዙ ሴት ሠራተኞች የተደፈሩ ስለመሆናቸው ከኢሴሕባማ እና ፍልሰት ዓለምአቀፋዊ ድርጅት (ፍዓአድ) የቀረቡ የሚታመኑ ዘገባዎች ነበሩ። በሰዎች ስለመነገድ (ክፍል 5ን ይመልከቱ)። በከፊል የተደፈሩ ኢትዮጵያውያን ሴት ሠራተኞችን ለመርዳት በማሰብ፣ በነሐሴ ወር መንግሥት በዱባይ አዲስ ቆንስላ ከፍቷል።

ሕግ መንግሥቱ ሁሉም ሰዎች በሕግ ፊት እኩል ናቸው ይላል። ሆኖም፣ እነዚህን ጥበቃዎች በሚገባ ለማስፈጸም መንግሥት/አስፈላጊ የሆኑትን ሁሉ አሚልቶ አላስቀመጠም። የቤተሰብ ሕግ የሴት ልጆች የጋብቻ ዕድሜ 18 ዓመት መሆኑን የወሰነ ሲሆን፣ ለወንድ ልጆችም ያው ሆኖ፣ የፍትሐብሔር ሕጉን ከልማዳዊ እና ሃይማኖታዊ ሕግ በላይ ያደርጋል። ለ5 ዓመታት ያህል አብረው ከኖሩ ያልተጋቡ ጥንዶች ንብረት በሕግ እንዲካፈሉ ይፈቅዳል፣ በፍርድ ቤት ሥርዓት ፋንታ የቤተሰብ (ቤተ ዘመድ) ዳኞች የጋብቻ አለመግባባቶችን መወሰናቸውን ያስወግዳል፣ የጋራ የሆኑ የጋብቻ ንብረቶችን በጋራ ማስተዳደርን ይፈቅዳል፣ ጋብቻ የሚፈርስ ወይም መለያየት የሚደርስ ከሆነ ፍርድ ቤቶች ለሕጻናት ወይም ለቤተሰቡ ደካማ አባል ልዩ ትኩረት እንዲሰጡ ይጠይቃል፣ ከጋብቻ መፍረስ ወይም ከባል መሞት በኋላ እንደገና ማግባት የሚፈልጉ ሴቶች 6 ወር እንዲጠብቁ ያሰግድዳል። ሆኖም፣ የክልል ምክር ቤቶች ለየክልላቸው የቤተሰብ ሕግ የመወሰን ሥልጣን ነበራቸው።

ከሕዝቡ 85% በሚኖርባቸው የገጠር አካባቢዎች በሴቶች ላይ የሚደረገው መድልዎ በጣም የከፋ ነበር። የፍትሐብሔር ሕግ እና የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ፣ ባል የቤተሰቡ ኃላፊ እና ዕድሜያቸው ከ5 ዓመት በላይ ለሆኑ ሕጻናት ብቸኛ ሞግዚት ነው እንደሚለው ያሉት የመድልዎ ድንጋጌዎች አሉባቸው።

የቤት ውስጥ ሁከት ፍቺ ለማግኘት አንድ ትልቅ ምክንያት ሆኖ አልተቆጠረም። አብሮ መኖር (ልማዳዊ ጋብቻ) ከሕጋዊ ጋብቻ እንደሚቆጠር የነበረው የሕግ እውቅና የተወሰነ ብቻ ነበር። ይህን የመሰለው ጋብቻ ለስንትም ያህል ረጅም ዓመታት ቢቆይ፣ ግንኙነቱ ሲቋረጥ ሴቲቱ የምታገኘው የሶስት ወር የገንዘብ ድጋፍ ብቻ ነበር። አንድ ባል ለቤተሰቡ የገንዘብ እርዳታ የማድረግ ኃላፊነት አልነበረበትም። በዚህም የተነሳ የጋብቻ ችግር ሲፈጠር አንዳንድ ጊዜ ባሎቹ ሴቶቹን እና ልጆቻቸውን ጥለው ይሄዳሉ። ሕጉ ከጋብቻ በፊት የነበረ/የተፈራ ማናቸውም ንብረት የዚያው ወገን ንብረት ነው ይላል። ማናቸውም ጋብቻው በቆየበት ጊዜ የተገኘ ንብረት ለባልና ለሚስት እኩል ይካፈላል። ስለዚህም አንድ ባሏ የሞተባት ሴት በጋብቻ ጊዜ ከተፈራው ንብረት 50% ድርሻዋን የመውሰድ መብት አላት። ሆኖም፣ አንድ ሚስት የሞተ ባሏን ድርሻ የመውረስ መብት የላትም።

መሬት በሙሉ የመንግሥት ነበር። ሴቶች መሬት ከመንግሥት መከራየት ቢችሉም፣ መንግሥትም ሴቶች በእኩልነት መሬት እንዲያገኙ ግልጽ ፖሊሲ ቢኖረውም፣ በገጠር ማኅበረሰቦች ዘንድ ይህ ፖሊሲ አስገዳጅነት አልነበረውም። ኢሴሕባማ በገለጸው መሠረት፣ ከሞላ ጎደል በሁሉም ክልሎች ሴቶች መሬት ማግኘት አይችሉም። መሬት መውረስም ስለማይችሉ፣ ባለመሬት መሆን የሚያስችላቸው ጋብቻ ብቻ ነበር። ሆኖም ግን፣ ባልየው ሲሞት በአብዛኛው ሌሎች የቤተሰብ አባላት መሬቱን ከሚስትየዋ ይወስዱባታል።

በገጠር አካባቢዎች ሴቶች ከወንዶች ያነሰ ለሥራ የመቀጠር ዕድል ነበራቸው። የተገኙት ሥራዎችም ለእኩል ሥራ እኩል ክፍያ አላሰገኙም።

በሴቶች ጉዳዮች ጠንካራ እንቅስቃሴ በሚያደርግ አንድ ስብስብ ተማፅኖ የኢትዮጵያ ብሔራዊ የምርጫ ቦርድ (ኢብምቦ) ኃላፊ በሐምሌ ወር ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የሴቶችን እጩነት በይፋ ተቀብሏል።

ሕጻናት

መንግሥት፣ ምንም እንኳን ለሕጻናት የተሻለ የጤና ክብካቤና መሠረታዊ ትምህርትን ለማዳረስ የአቅም ውስንነት ቢኖርበትም፣ በሕጻናት ማኅበራዊ፣ የጤና፣ እና የሕግ ጉዳዮች ላይ የሚያተኩሩ አገር በቀልና ዓለምአቀፋዊ መያዶችን እንቅስቃሴ ደግፏል።

እስከ 6ኛ ክፍል ድረስ መማር ግዴታ ነው። የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ከክፍያ ነጻ መሆኑ በሕግ ተደንግጓል። በዓመቱ ውስጥ ተጨማሪ ት/ቤቶች ቢገነቡም፣ የአገሪቱን ወጣቶች ማስተናገድ በሚችሉበት ቁጥር አላደጉም። ይህ ችግር በተለይ በገጠሪቱ ኢትዮጵያ የተባባሰ ነው። በተጨማሪም የተማሪዎች የደንብ ልብሶች፣ መጻሕፍትና የመማሪያ ቁሳቁስ ዋጋ ለብዙዎቹ ወላጆች የሚቀመስ አልነበረም። የመማሪያ ክፍሎችን አሟጦ ለመጠቀምና እየሠሩ ለሚማሩ ወጣቶች ዕድል ለመስጠት እንዲያስችለው፣ መንግሥት በአብዛኛዎቹ የከተማ የአንደኛና የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች ውስጥ የሶስት ፈረቃ የትምህርት ሥርዓትን ተጠቅሟል። በ1994 ዓ.ም. 43% የአንደኛ ደረጃ ት/ቤቶች እና 70% የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች ያህል የሚሆኑት ያሏቸውን የመማሪያ ክፍሎች በሚገባ ለመጠቀም የሁለት ፈረቃ ሥርዓ ትን ተጠቅመዋል። የአንደኛ ደረጃ የትምህርት ዕድል ማግኘት ከሚገባቸው ወጣቶች መካከል ከወንዶች 74.4% እና ከሴቶች 59.1% ብቻ የትምህርት ዕድል አግኝተዋል። ከአዲስ አበባ በስተቀር ወደ ት/ቤት ከሚሄዱት ወጣቶች መካከል የሴት ተማሪዎች ቁጥር ከወንድ ተማሪዎች ቁጥር ያነሰ ነው። አዲስ አበባ ውስጥ ግን የሴት ተማሪዎች ቁጥር ከወንዶቹ በ52.9% ከፍ ብሏል። ከተመዘገቡት ተማሪዎች መካከል 28.7% የሚሆኑት ትምህርታቸውን በማቋረጣቸው ወደ 2ኛ ክፍል አለማለፋቸውን የመንግሥት ዘገባዎች አመልክተዋል። አንደኛ ክፍል ከጀመሩ ተማሪዎች መካከል 22.1% ብቻ 8ኛ ክፍልን አጠናቀዋል። በ1993 ዓ.ም. በተደረገ የሕጻናት ከመሥራት የመጠበቅ ዳሰሳ ጥናት መሠረት በአገሪቱ ውስጥ ከሴቶች 20.6% ብቻ ማንበብና መጻፍ ይችላሉ። የወንዶቹ ግን 42.7% ነው።

የወጣት አጥፊዎችንና የተጠቁ ወጣቶችን መብቶች ለመጠበቅ የሚያስችሉ በአንድ መንግሥታዊ ባልሆነ ድርጅት አባላት ሠራተኞች የሚንቀሳቀሱ 10 የወጣት ማስተናገጃ ማዕከላት በአዲስ አበባ ፖሊስ ጣቢያዎች ስር ይገኛሉ። የተወሰኑ የፖሊስ

መኰንኖች የወጣት አጥፊነትንና የሕጻናት መብት ረገጣን በሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ ሥልጠና አግኝተዋል።

የልጃገረዶች መደፈር ችግር እንደቀጠለ ነው። በአብዛኛዎቹ ልጃገረዶች ላይ ግርዛት ተካሂዶባቸዋል (በክፍል 5 ስለሴቶች የቀረበውን ዘገባ ይመልከቱ)። ሌሎች ከጉጂ ባህል ጋር የተያያዙ እንደ እንጥል ማስቆረጥ፣ ግማ ማውለቅ፣ ለአቅመ ሄዋን ሳይደርሱ መዳር፣ በጠለፋ ማግባት፣ እና ምግብና ሥራ መከልከል ገና አልቆሙም። (ክፍል 5 በሰው ስለመነገድ የቀረበውን ይመልከቱ)::

በአገሪቱ ምሥራቅ በሚገኘው የአፋር ክልል ወጣት ልጃገረዶች በጣም ታላቃቸው ለሆኑ ወንዶች መዳራቸው ቢቀጥልም፣ ይህንን አስከፊ ባሕል ማስወገድ ልዩ ትኩረት ያገኘ ሲሆን፣ የሰላ ሒስም ቀርቦበታል። በተጨማሪም ጉጂ ባሕልንና ለአቅመ ሔዋን ሳይደርሱ መዳርን በሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ ማኅበረሰቡን ከአጉል አመለካከቱ ለማላቀቅ እንደ ከምባታ ሴቶች ራስ ገዝ ማዕከልና የትግራይ ሴቶች ማኅበር ያሉት አገር በቀል መያዶች የችግሩን ስፋትና ጥልቀት ማስገንዘብ መቻላቸውን መገናኛ ብዙሃን ዘግበዋል። ከአንድ የገጠር ወረዳ በየካቲት ወር የቀረበ ዘገባ እንደገለጸው በት/ቤቶችና በአካባቢው ባለሥልጣናት ጥረት ዕድሜያቸው በ9 ዓመት ያህል የተወሰነ ለጋብቻ ያልደረሱ 74 ወጣቶችን ከመዳር አስጥሏል። በዝቅተኛ ዕድሜአቸው ያረገዙ ኮረዶች ብዙውን ጊዜ የፊስቱላ መቀደድና ቋሚ የሽንት መቋጠር ችግር ደርሶባቸዋል። ለዚህ ችግር ሕክምና የሚሰጥና በዓመት 1,000 የፊስቱላ ቀዶ ሕክምና የሚያደርግ አንድ ሆስፒታል ብቻ በአዲስ አበባ ይገኛል። በሆስፒታሉ ግምት መሠረት፣ ለእያንዳንዱ የተሳካ የቀዶ ሕክምና 10 ሌሎች ወጣት ሴቶች ሕክምና ይሻሉ። በነፍሰ ጡሮች የምግብ ዓይነት ክልከላዎች፣ በድህነት፣ ዕድሜያቸው ለጋብቻ ሳይደርስ ከመዳር፣ እና ከግርዛት ጋር በተያያዙ የወሊድ ችግሮች የተነሳ በወሊድ ምክንያት የሚሞቱ ሴቶች ቁጥር እጅግ ከፍተኛ ነው።

ያልተረጋገጡ ዘገባዎች እንዳመለከቱት ከአገሪቱ ደቡባዊ ክፍል በጉዲፈቻ ቀለበት በሚንቀሳቀሱ ግለሰቦች አማካይነት የተወሰኑ ሕጻናት ወደ ኬንያ ተወስደው የሌሎች ብሔረሰቦች የማደጉ ልጆች ሆነዋል።

ዕድሜያቸው ለአቅመ ሔዋን ያልደረሱ ወጣቶች ሴትኛ አዳሪነት እንደቀጠለ ሲሆን፣ ችግሩም እየተባባሰ ለመሄዱ ግንዛቤ አለ። ሥርዓት በአለው መንገድ በተካሄደ ጉዲፈቻ አማካይነት ሕጻናት ከአገር መውጣታቸውን አንዳንድ ዘገባዎች አመልክተዋል (በክፍል አምስት በሰው ስለመነገድ የቀረበውን ዘገባ ይመልከቱ)።

ሕጻናትን ማሠራት አሳሳቢ ችግር እንደሆነ አለ (ክፍል 6. መን ይመልከቱ)።

በመንግሥት ይፋ ግምት መሠረት አዲስ አበባ ውስጥ የሚገኙትን ከ50,000 እስከ 60,000 የሚሆኑትን ጨምሮ፣ በአገሪቷ ውስጥ ከ150,000 እስከ 200,000 የሚደርሱ የጐዳና ተዳዳሪዎች ይገኛሉ። ከ100,000 በላይ የሆኑ የአዲስ አበባን ጨምሮ፣ በአገሪቱ ውስጥ ወደ 600,000 የሚጠጉ የጐዳና ተዳዳሪዎች ሳይገኙ እንደማይቀር ዩኒሴፍ (የተመድ የሕጻናት መርጃ ድርጅት) ገምቷል። በወላጆች የአልጋ ቁራኛ መሆንና በቤተሰብ ገቢ መቀነስ የተነሳ ችግሩ ከጊዜ ወደጊዜ እየተባባሰ መሄዱን ዩኒሴፍ ያምናል። እነዚህ የጐዳና ተዳዳሪዎች፣ አንዳንድ ጊዜ ተሰባስበው ይለምናሉ፣ ወይም ያገኙትን ሥራ ይሠራሉ (ክፍል 6. መን ይመልከቱ)። ቁጥራቸው በርካታ በመሆኑ ምክንያት ያሉት መንግሥታዊና የግል እንጦ መውታን ተንከባካቢዎች የጐዳና ተዳዳሪ ሕጻናትን ችግር መቅረፍ አልቻሉም፣ ይባስ ብሎ ትልልቆቹ ልጆች ትንንሾቹን ይበድላሉ። በጣም አሳሳቢ በሆነ ድህነት ምክንያት ተጥለው የተገኙ ሕጻናት በሆስፒታሎችና እንጦ ማውታን ተንከባካቢ ተቋሟት ተገቢው ክብካቤ አይደረግላቸውም። በልመና የገቢ ምንጫቸውን ለማሳደግ ታጥቀው የተነሱ "አሰማሪዎቻቸው" አንዳንድ ጊዜ የሕጻናቱን አካል ያጐድላሉ፣ ዓይናቸውንም ያሳውራሉ።

በሰዎች መነገድ

በሰዎች መነገድ በሕግ የተከለከለ ነው። ሆኖም፣ ሰዎች ወደ አገሪቱ፣ ከአገሪቱ ውጭና በአገር ውስጥ በመነገጃነት ስለመጓዛቸው በርካታ ዘገባዎች ነበሩ። ለአቅመ ሔዋን ያልደረሱ ወጣቶች በሴትኛ አዳሪነት መሰማራት በተለይ በከተሞች አካባቢ አሳሳቢ ችግር ነበር። የወንጀለኛ መቅጫ ሕጉ የሚከለክለው ሴቶችና ልጆች ለሴትኛ አዳሪነት እንዳይነገድባቸው ነው። ይህን የመሰለው በሰዎች መነገድ እስከ 5 ዓመት የሚደርስ እስራትና 1,150 የአሜሪካ ዶላር (ብር 10,000) የገንዘብ ቅጣት